# አናነባም፣ አናለቅስም፣ አንጮህምም…

እስክንድር አለማየሁ

ስለምን እናነባለን! ስለምንስ እናለቅሳለን! ምን ሆነንስ እንጮሃለን! ጥቂቶች በወቅቱ የነበረው ጭቆና ታይቷቸው በሕዝቦች ላይ የተንሰራፋው አገዛዝ አስመርሯቸው ወደ በረሃ በመግባት ብዙኃንን ከጎናቸው አሰልፈው ከመራራ ትግል በኋላ ሥርዓቱን በመገርሰስ ለድል በቅተዋል፡፡

ይህ ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለነፃነት፣ ለሠላምና ዴሞክራሲ የተደረገ ትግል የብዙኃንን ህይወት የጠየቀ ቢሆንም ፍፃሜው ዛሬ ላሉት ሕዝቦች የማይነቃነቅ መሠረት ጥሏል፡፡

ዜጎች ኑሮአቸውን እንዴት እንደሚተፉ የተቸገሩበት፣ ተስፋቸው ተሟጥጦ ግራ የተጋቡበት፣ መቋጫ በሌለው ጦርነት፣ ረሃብና ስደት የሚንገላቱበት ያ ወቅት ደግሞ ላይመለስ ሄዷል … እናም ስለምን እናነባለን!

ዜጎች ዛሬ ለአዲስ ሕይወት ማበብ ተስፋ ሰንቀው ኑሮን ማጣጣም ይዘዋል፡፡ ሠላማዊ አየር መተንፈስ፣ ሰርቶ መግባትና በነፃነት መንቀሳቀስ ችለዋል፡፡

ለዚህ መብቃት የተቻለው ራዕይ ባለው መሪ አመራር ሰጪነትና ሺህዎች በከፈሉት የሕይወት መስዋዕትነት በተገኘው ዴሞክራሲያዊ ሂደት ነው፡፡

ጨቋኝ አምባገነናዊ ሥርዓት ተገርስሶ በሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ የመንግሥት ሥልጣን የሚረከቡበት አገር መፍጠር ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በደማቸው ቀለም የፃፉት ህገ መንግሥት በጠንካራ መሠረት ላይ ለተገነባው አንድነት ዋስትና ሆኗቸዋል፡፡ በልማት ማማ ላይ መወጣጣትን ይዘዋል፡፡

ህገ መንግሥቱ ለሕዝቦች ካጎናፀፈው ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባሻገር ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በፍቃዳቸው በመሠረቷት አንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ አካባቢያቸውን ለማሳደግ ዕድል ከፍቶላቸዋል፡፡

በመሆኑም ዜጎች አንገታቸውን ቀና አድርገው በራስ መተማመን መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዘው ዓለምን በሚያስደንቅ ሁኔታ ዕድገት በዕድገት ላይ በማስመዝገብ ጉዟቸውን ተያይዘውታል - እናስ ስለምን እናለቅሳለን!

ህገ መንግሥታችን የዜጎች ዋስትና ነው የሚባለው ያለምክንያት አይደለም፡፡ የኃይማኖት እኩልነትን ያረጋገጠ፣ በዜጎች መካከል መተማመንን የፈጠረ፣ ሕዝቦች በሀገራቸው ጉዳይ በእኩልነት ተሳታፊና ወሣኝ እንዲሆኑ ያስቻለ፣ በሀገራቸው ሀብት የበይ ተመልካኝ ሣይሆኑ በፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ተጠቃሚ ያደረገ ነው፡፡

ሌላው ህገ መንግሥታችን የዜጎች ዋስትና ነው የሚባለውም ዜጎች በሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ተደራጅተው ይጠቅመናል ብለው የሚያስቡትን አማራጭ ይዘው በመወዳደር የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ዕድል ስለከፈተላቸው ነው - እናስ ስለምን እንጮሃለን!

ዛሬ በኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋቸውን በሚናገሩና ባህላቸውን በሚያከብሩ፣ እምነትና ወጋቸውን በሚያውቁና በሚያስከብሩ፣ ራሳቸው በመረጧቸው አመራሮች ነው የሚተዳደሩት፡፡

ህገ መንግሥቱ ካስቀመጣቸው መርሆዎች ውጪ በቸልተኝነት ሕዝብ የጣለባቸውን አደራ በብቃት የማይወጡትን ውክልናቸውን የማንሳት ህገ መንግሥታዊ መብት ጭምር በእጃቸው ጨብጠዋል፡፡

ክብር ለባለራዕዩ መሪያችንና ለትግሉ ሰማዕታት ይሁንና የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ጥቅሞቻቸውን በማጎልበት አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመገንባት ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ በአንድነት ተነሳስተዋል፡፡

በብዝሃነት ላይ መሠረቱን የጣለው አንድነት ለህዳሴውም ስኬት መገለጫ ነውና የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህገ መንግሥት ጠብቆ ለማቆየት ሁሉም በፅናት ቆሟል፡፡

ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩበት፣ ለዴሞክራሲያዊ አንድነት መሠረት የተጣለበት፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት፣ ውበትና ህብረት የታየበት ብሎም የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤት መሆናቸውም የተረጋገጠበት፣ የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዞ የተጀመረበት መሠረቱ ይኸው ህገ መንግሥትና ለህገ መንግሥቱ ዘብ የቆመ ጠንካራ አመራርና ሕዝብ ነው፡፡

የህገ መንግሥቱ ድሎችና ውጤቶች ከመቼውም በላይ ተስፋፍተው፣ የዜጎች ማንነትና ባህላዊ እሴቶች ጎልተው ወጥተው፣ መልካም ተሞክሮዎችም ይበልጡን ጎልብተው፣ የአንድነታችንና የጥንካሬያችን መገለጫ ሆነው እንዲቀጥሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው ጉዟቸውን ቀጥለዋል፡፡

በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው እኩል የመልማት መብት በመጠቀም በሁሉም ክልሎች በተነፃፃሪ ፈጣን የሚባል የልማት ዕድገት ተመዝግቧል፡፡

በአፈፃፀም ሂደት የተገኙ በጎ ልምዶችም እየተቀመሩ በአገሪቱ ሁሉም አካባቢዎችና ለምልዓተ ሕዝቡ የሚደርስበት ሥልት ተቀይሶ ትልቅ ውጤት እንዲመዘገብ አስችሏል፡፡

የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመተግበር ዙሪያ የሚያጋጥሙ ማነቆዎች የሚለዩበትን የአሠራርና የአደረጃጀት ጥያቄዎች ካለፉት ልምዶች በመነሳት እንዲፈተሹና እንዲስተካከሉ በማድረግ የሕዝቦች የላቀ ተሣትፎና ተጠቃሚነት እየተረጋገጠ ይገኛል፡፡

ክልሎች በገጠርና ከተማ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶችን በመንደፍና ሕዝቦቻቸውን ዋና ተዋናይ፣ ፈፃሚና አስፈፃሚ በማድረግ ላለፉት ስምንት ዓመታት በአማካይ ለተመዘገበው 11 በመቶ ዕድገት የድርሻቸውን አበርክተዋል፡፡ ውጤቱንም ማጣጣም ጀምረዋል፡፡

በዚህ ላይ በመንተራስ ባለራዕዩ መሪያችንና የሚመሩት ፓርቲ የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበር ከጀመሩ ሁለት ዓመታትን አሳልፈዋል፤ በጎ ጅማሮዎችንም አይተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ይህን ከኋላ ቀርነትና ከልመና የሚያላቅቃቸውን የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ለተግባራዊነቱ ሌት ተቀን በአንድነት የሚተጉት ያለምክንያ
ት አይደለም፡፡ ባለፉት ዓመታት የወጡት ፖሊሲዎችና የተቀየሱ ስትራቴጂዎች ብዙኃንን ተጠቃሚ አድርገው በማየታቸው ጭምር ነው፡፡

ባለራዕዩ መሪያችን የሀገራችንን ህዳሴ እውን ለማድረግ ከቀረፁት የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በዋናነት የሚጠቀሱ ብዙ ዘርፎች ቢኖሩም የሀገሪቱን ዕድገት ተከትሎ

የሚመጣውን የኃይል ፍላጎት ጥያቄ በተሟላ ሁኔታ ለመመለስ እንዲችሉ ተደርገው የተጀመሩ የኃይል መስጫ ጣቢያዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከ21 ዓመታት በፊት ከ500 ሜጋ ዋት በታች የነበረው የኢትዮጵያ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች አቅም በተሰጠው ቁርጠኛ አመራር በአሥርና ሃያ እጥፍ እንዲያድግ መሠረቱ ተጥሏል፡፡

የሀገራችንን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነት የበለጠ ያስተሳሰረውና የጠቅላይ ሚኒስትራችንን ህያውነት የሚያረጋግጠው የህዳሴው ግድብ የታላቅነታችን መገለጫ እንደሚሆን ሕዝባችን አንዳች ጥርጥር የለውም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኃይል አቅርቦታቸውን የበለጠ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን ከማረጋገጣቸውም በላይ የሚተርፋቸውን ኃይል ለጎረቤት ሀገራት በመሸጥ ከሚያገኙት ምጣኔ ሀብታዊ ተጠቃሚነት በላይ ከጎረቤት ሀገራት ጋር አብሮ ተደጋግፎ የመልማትን አስተሳሰብ በማስረፅ ለአካባቢያችን ሠላምና መረጋጋት ዓይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ሌላው የሀገራችንን ህዳሴ እያረጋገጠ ያለውና ለዘመናት በመጠሪያነት የነበረውን ስም የቀየረው ለግብርና ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት ነው፡፡

ግብርናችን ከእጅ ወደ አፍ ከነበረው አካሄድ ተላቆ በሰለጠኑ ባለሙያዎች ውጤማነቱ በተረጋገጠ ግብዓት ላይ በመመስረት ወደ ገበያ መር ግብርና እየተሸጋገረ ያለውም በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

የገጠሩ ህዝብ ህይወት ሊቀይር የቻለውም የግብርናው ዘርፍ እንደ ከዚህ ቀደሙ በተወሰኑ ምርቶች ላይ የተንጠለጠለ ባለመሆኑ አርሶ አደሩ ከአካባቢው ጋር ሊስማማ የሚችለውን ሥራ በመምረጥ አዋጭነቱን በማስጠናት በስፋት እንቅስቃሴ በመጀመሩ ነው፡፡

በዚህም በጥቂት ዓመታት ብዙ የልማት ጅግኖችን ለማግኘት ተችሏል፡፡ መንግሥት የእነዚህን የልማት ጀግኖች ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋት በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍል ተስፋፍቶ የነበረውን ድህነት ለመቀነስ ችሏል።

በተጨማሪም አርሶ አደሩ ከዚህ ቀደም ሞክሯቸው የማያውቀውን የአበባ፣ የቅመማ ቅመም፣ የፍራፍሬ የሥጋ፣ የቅባት እህሎችና የቆዳና ሌጦ ምርቶችን በማምረት እሴት ጨምሮባቸውም ሆነ ሳይጨምርባቸው ለዓለም ገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ጥቅም ለማግኘት ችሏል።

የግብርናው ዘፍር ዕድገታችን ከኤክስፐርት ባሻገር ለሀገራችን ኢንዱስትሪዎች ፋብሪካዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ አንቀሳቃሾች በበቂ ሁኔታ ግብዓትን

በማቅረብ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ በብቃት ከማስቀረቱም በላይ ዜጎች ሥራ ፈጥረው ራሳቸውንና ሀገራቸውን ለመጥቀም ደፋ ቀና ለሚሉት ዕድልን ከፍቷል።

ባለ ራዕዩ መሪ ባስቀመጠው ዕቅድ መሠረት የግብርና ዘርፍ ግብ በምግብ ምርት ራሳችንን በራሳችን መቻል ቢሆንም በተያያዥነት የገጠሩ ህዝባችንን አኗኗርም መቀየር ነው።

በዚህም ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየታዩ ነው፡፡ ሣር ቤት፣ በቆርቆሮ ክዳን፣ ኩራዝ በአምፖል፣ ለመኝታና ለመቀመጫ የሚጠቀሙበት መደብ በወንበርና በአልጋ፣ ተቀይረው ለማየት ተችሏል።

ዛሬ በገጠሩ የሀገራችን ክፍል ለቴሌቪዥን ዜና መከታተልና መዝናናት አዲስ ነገር መሆኑ አብቅቷል፡፡ መልዕክት በቃል መላላኩ ቀርቶ መረጃ በሞባይል ወደ መለዋወጥ ተሸጋግሯል፡፡

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ትናንት ዋና ዋና ከተሞችን ብቻ እርስ በርስ ያገናኝ የነበረው የመንገድ ልማት ዘርፍ ተመልካችን በሚያስደምም መልኩ በስፋትና በጥራት በልማት ኋላ ቀርተዋል ተብሎ ሲጠቀሱ እስከነበሩ አካባቢዎች በመድረስ የሕዝቦችን ተጠቃሚነት አረጋግጧል።

የጤና ዘርፉም ቢሆን በጣት ይቆጠሩ ከነበሩ የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተቋማት እንቅስቃሴ ተላቆ በብዙ ሺህዎች ወደሚቆጠሩ የጤና ኬላዎች፤ ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች አገልግሎቱ በአጭር ጊዜ ለመድረስ ችሏል፡፡

ዜጎች በአካባቢው፣ በቤቱ የበሽታ መከላከል እውቀቱን እንዲያዳብር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎችን በማሰልጠን ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ተደርጓል።

ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች በታሪክ አጋጣሚ በድንበር ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ምንም ዓይነት የሰው ኃይል፣ የማህበራዊና ምጣኔ ኃብታዊ ልማትና የመሠረተ ልማት አውታሮች ያልተሞከረባቸው አካባቢዎች ናቸ፡፡ አገሪቱ በአጠቃላይ ከተዘፈቀችበት ድህነትና ኋላ ቀርነት በባሰ ደረጃ ሥር ሰዶ የቆዩባቸው አካባቢዎች ነበሩ።

እነዚህ ክልሎች በአሁኑ ወቅት ፖለቲካዊ መብታቸው እንደተቀሩት ክልሎች አስከብረው የእድገትና ትራንስፎሚሽን ዕቅዱ ውጤት ተጠቃሚ እየሆኑ ነው። የሰው ኃይል ልማት በራሳቸው በፌዴራሉ መንግሥት እገዛ እየተሟላላቸው ነው።

የትምህርት ፖሊሲወም እያደገ እየመጣ ያለውን የሀገራችንን ኢንዱስትሪ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል መልኩ የተቀረፀ በመሆኑ ዛሬ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በብዛት ተማሪዎችን እየተቀበሉ በማሰልጠን ለልማታቸው አጋዥ ኃይል እየፈጠሩ ይገኛሉ።

ዛሬ ሀገራችን ከየትኛውም ጊዜ በላይ ሠላማዊ ሆናለች፡፡ የመሠረተ ልማት ዝርጋታው፣ የጤና ተቋማት አቅርቦት፣ የትምህርት ተቋማት ተደራሽነት ወደ ላቀ ደረጃ እየተሸጋገረ ያለበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው።

በዚህም ተበረታትተው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ ለአገራችን ዕድገት ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቷ እያደገ በምሣሌነት እየተጠቀሰች ነው።

ታዲያ ይህን በብልሁ መሪያችን የተጀመረውንና ዓለምን እያነጋገረ የሚገኘውን ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ዕድገት በማስቀጠል የሀገራችን ህዳሴ መሠረት የሆኑትን ታላቁ መሪያችንን ህያውነት ማረጋገጫ ተግባራትን ማስቀጠል ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠበቃል።

ዛሬ በታላላቅ ድሎቻችን ታጅበን ህገ መንግሥታችን በሰጠን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተጠቅመን አንገታችንን ከፍ ማድረግ ጀምረናል፡፡ በመሆኑም አናነባም! አናለቅስም! አንጮህምም!

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተጀመሩ ተስፋ ሰጪ የአንድነታችን መሠረቶች፤ የጠቅላይ ሚኒስትራችን ማስታወሻዎች ሆነው እንዲቀጥሉ መላው ሕዝብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ሂደቶቹን በፍጹም ስኬታማነት ማስቀጠል ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ሲሆን የገባነውን ቃል ጠብቀናልና አናነባም! አናለቅስም! አንጮህምም!